# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

# Commercial Bank of Ethiopia

## በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚከፍቱት ሂሣብ

*አስተማማኝ በሆነው የአገርዎ ባንክ ገንዘብዎን ያስቀምጡ!*

## በውጭ ምንዛሪ የሚከፈት ተቀማጭ ሂሣብ

* ይህ አገልግሎት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የውጭ ምንዛሪ ተቀማጭ ሂሣብ አገራቸው በሚገኝ ባንክ እንዲከፍቱ ያግዛል፡፡
* ይህን ሂሣብ ግለሰቦች እንዲሁም ዋና መሥሪያ ቤታቸው ውጭ ሀገር የሚገኙ ድርጅቶች መክፈት ይችላሉ፡፡
* ሂሣቡን መክፈት የሚቻለው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የውጭ አገር ገንዘቦች ብቻ ነው፡፡
  - የአሜሪካን ዶላር፣
  - የእንግሊዝ ፓውንድ፣
  - ዩሮ
* ሆኖም ባንኩ በሚሰራባቸው የውጭ አገር ገንዘቦች ለምሳሌ በካናዳ ዶላር፣ በጃፓን የን፣ በሳዑዲ ሪያል፣ በአውስትራሊያ ዶላር እና በዩናይትድ አረብ ኢምሬትስ ድርሃም የሚላክ ገንዘብ ከላይ ከተጠቀሱት ከሶስቱ የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች ወደ አንዱ ተመንዝሮ ወደተከፈተው ሂሳብ ገቢ ይሆናል፡፡

## የተቀማጭ ሂሣብ ዓይነቶች

### በጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ፣

* ለተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚቀመጥና ወለድ የሚከፈልበት ሂሳብ ነው፡፡
* አነስተኛው የጊዜ ገደብ ሦስት ወራት ነው፡፡
* ሒሳቡን ለመክፈት የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ገንዘብ 5,000 የአሜሪካን ዶላር ወይም ከላይ ለተጠቀሱት የውጭ ገንዘቦች ተመጣጣኙ እየተሰላ ይሆናል።
* ወለድ ተከፋይ የሚሆነው ተቀማጭ ሂሳቡ ለተከፈተበት አነስተኛ የጊዜ ገደብ ተቀምጦ ሲቆይ ብቻ ነው፡፡
* ከዚህ ሂሣብ የሚገኘው የወለድ ገቢ ከግብር ነፃ ነው፡፡
* ሒሳቡ ከተከፈተና ገንዘቡ ከተላለፈ በኋላ ባንኩ ለደንበኛው ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ይሰጣል፡፡

### 1. ተንቀሳቃሽ ሂሣብ፣

* በማንኛውም ወቅት ቼክ በመፃፍ ገንዘብ ከዚህ ሂሣብ ወጪ ማድረግ ይቻላል፡፡
* ይህንን ሂሣብ ለመክፈት የሚያስፈልገው አነስተኛው ተቀማጭ ገንዘብ መጠን 100 የአሜሪካን ዶላር ወይም የዚህ ተመጣጣኝ በሆነ ዩሮ፣ የእንግሊዝ ፓውንድ ወይም ባንኩ በሚሠራባቸው የውጭ አገር ገንዘቦች ነው፡፡
* በዚህ ሂሣብ ላይ ለአስቀማጩ ወለድ አይከፈልም፡፡
* ከዚህ ሂሣብ ላይ በውጭ ምንዛሪ ወጪ ማድረግ የሚቻለው የሂሳቡ ባለቤት ከኢትዮጵያ ውጭ እንደሚጓዝ የሚያረጋግጡ ሰነዶች ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡
* ከዚህ ሂሣብ ላይ የውጭ ምንዛሪ ከኢትዮጵያ ውጪ ማስተላለፍ/መላክ ይቻላል፡፡

### 2. ወደ ውጭ አገር ሂሣብ ወይም ገንዘብ መዘዋወር የማይችል ሂሳብ

* ይህ ሂሣብ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ ገንዘብ ተቀይሮ በብር የሚቀመጥና የአገር ውስጥ ክፍያዎችን ለመፈፀም የሚያገለግል ነው፡፡
* በዚህ ሂሣብ ተቀማጭ የሚሆን ገንዘብ በዕለቱ ባለው የውጭ ምንዛሪ መጠን ተሠልቶ ወደ ብር ተቀይሮ ተቀማጭ ይሆናል፡፡
* በዚህ ሂሣብ ላይ ለአስቀማጩ የሚከፈለው ወለድ ከመደበኛው የተቀማጭ ሂሣብ ወለድ እጥፍ ይሆናል፡፡
* በማንኛውም ወቅት ቼክ በመፃፍ ገንዘብ ከዚህ ሂሣብ ወጪ ማድረግ ይቻላል፡፡
* ከዚህ ሂሣብ በውጭ ምንዛሪ ገንዘብ ማውጣት አይቻልም፡፡

**የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች**

በውጭ ምንዛሪ የሚከፈት ተቀማጭ ሂሳብ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት፣

* በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣
* በውጭ አገር የሚኖሩ በትውልድ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች፣
* ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ነገር ግን በሥራ ምክንያት በውጭ አገር ከአንድ ዓመት በላይ የኖሩ እንዲሁም በውጭ ሀገር ከአንድ አመት በላይ ለሚቆይ ሥራ የሚጓዙና ለዚህም በቂ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ናቸው።

**የሂሣብ አከፋፈት**

* ከላይ የተጠቀሱትን የሚያሟሉ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግንባር ቀርበው ይህንን ሂሣብ መክፈት ይችላሉ፡፡
* በግንባር መቅረብ የማይችሉና ይህንን ሂሣብ መክፈት የሚፈልጉ አመልካቾች ማንነታቸውን ለማረጋገጥ በያሉበት አገራት ባሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ በኩል ሒሳቡን መክፈት ይችላሉ፡፡
* የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው ግለሰቦች በወካያቸው ስም ይህንን ሂሣብ መክፈት አይችሉም፡፡ ነገር ግን የውክልና ስልጣን ማስረጃቸው ላይ በግልጽ የተቀመጠ ከሆነ ይህንን ሂሣብ በወካያቸው ስም ማንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡

**አስፈላጊ ሠነዶች፣**

* በትክክል የተሞላ በሂሣብ ከፋቹ የተፈረመ የማመልከቻ ቅጽ፣
* ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያዊነት ፓስፖርትና የሚኖሩበት አገር የመኖሪያ ፍቃድ፣
* በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው ዜግነት የወሰዱበት አገር ፓስፖርትና በትውልድ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ፡፡

**ሂሣቡ የሚዘጋባቸው ሁኔታዎች፣**

ይህ ሂሣብ ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ከዛ በላይ በሆኑት ምክንያቶች ሊዘጋ ይችላል፡፡

* አስቀማጩ ሂሣቡ እንዲዘጋለት ጥያቄ ሲያቀርብ፣
* አስቀማጩ የውጭ አገር ቆይታውን አጠናቆ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ፣
* ሂሳቡ በዜሮ ባላንስ ከአንድ ወር በላይ ሲቆይ ሲስተሙ ወዲያውኑ ሂሳቡን የሚዘጋው ይሆናል፡፡

**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ**

**ሁሌም የሚተማመኑበት ባንክ!**


ስልክ:-251-11-551-95-06/251-11-515-66-61/251-115 51 24 37

ፋክስ: 251-11-551 78 22/251-11 554-62-43

ፖ.ሣ.ቁ. 255

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

የስዊፍት አድራሻ:- CBETETAA

ኢሜይል: cbe_swift@combanketh.et

cbediaspora@combanketh.et

ድረ ገጽ: www.combanketh.et


የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

Commercial Bank of Ethiopia